# ሞንትጎመሪ ካውንቲ የትራንስፖርት መምሪያ
# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ሁሉአቀፍ የአውቶብስ ስርጭት ጥናት፡-
# “ራይድ ኦን በአዲስ መልክ”

## መግቢያ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የራይድ ኦን አውቶብስ ስርዓት፣ በካውንቲው ውስጥ ለሚኖሩ እና ለሚሰሩ ሰዎች ወሳኝ ሚና የሚጫወት የመጓጓዣ አገልግሎትበመስጠት፣ ከ 40 ዓመታት በላይ አገልግሎት ሲሰጥ ነበር። ከዓመታት በኋላ፣ የራይድ ኦን የአውቶብስ መዋቅር ተለዋዋጭ ከሆነ የሥነ-ሕዝብ አወቃቀር እና የመሬት አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ሲቀያየር ነበር። ካውንቲው አሁንም ቢሆን የሕዝብ ብዛት፣ የሥነ ሕዝብ፣ የቅጥር ማዕከላት፣ እና መኖሪያ ቤቶች ለውጥ እያሳየ ይገኛል፣ በዚህም የተነሳ ስርዓቱን እንደ አዲስ ሙሉ ለሙሉ የመፈተሻ ጊዜው አሁን ደርሷል። በተለይ ከኮቪድ-19 ጋር በተያያዘ አስቀድመው ከተገመቱ ለውጦች ምክንያት ነው።

የአውቶብስ ጉዞ በአዲስ መልክ ሁሉን አቀፍ ጥናት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ ለወደፊቱ እና ለአሁኑ ፍላጎቶች መጓጓዣዎች እንዴት እንደሚንቀሳቀሱ የሚያሳዩ ወሳኝ የሆኑ ለውጦችን ሊያመጡ የሚችሉ መጪውን ጊዜ ከግምት ውስጥ የሚያስገቡ የአውቶብስ ስርጭትን የሚገመግም ነው። ይሄ ጥናት በካውንቲው ወሰኖች ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የሜትሮባስ አገልግሎቶች እና የወደፊቱን ፐርፐል ላይን ጨምሮ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲን ነባሩን እና የታቀደውን የመጓጓዣ ስርዓቶችን በጥልቀት ይመለከታል። በተጨማሪም መረጃዎችን በመተንተን እና ማህበረሰቡን በማሳተፍ የወደፊቱን የራይድ ኦን አቅጣጫ የማስቀመጥ ዕድልን ይፈጥራል። ለሁለቱም የራይድ ኦን እና ለሜትሮ አውቶብስ አገልግሎቶች ላይ አገልግሎት የሚሰጠውን ማህበረሰብ የአሁኑን እና የወደፊት ፍላጎቶች የሚያሟላ መላውን ስርዓት የሚቀይር ምክረ ሐሳብ ማስቀመጥ የጥናቱ ቀዳሚ አላማ ነው።

ጥናቱ የራይድ ኦን አገልግሎት መስጫ ቦታን የአሁኑን እና ለወደፊቱ ይከሰታሉ ተብለው የሚጠበቁ ሁኔታዎችን ይገመግማል፣ እንዲሁም የመጓጓዣ አማራጮችን መሰረት ለመገንባት የማህበረሰብ መሪዎችን፣ ተሚጋቾችን፣ ተጓዥ ተሳፋሪዎችን እና ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች ያሳትፋል። የመጓጓዣ ስርጭት መንገዶችን፣ ግንኙነቶችን፣ ሽፋን እና የአገልግሎት አቅርቦት ብዛት ላይ የገበያ ጥናት እና ትንተና፣ የመሬት አጠቃቀም ልማት እና ለወደፊቱ እንደሚከሰቱ የሚጠበቁ የቴክኖሎጂ ልቀቶችን የሚገመግሙ ሙሉ ምዘናዎች ይካሄዳሉ። በተጨማሪም የዘር እኩልነት እና የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል ካውንቲው ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ግቦችን ከግምት ውስጥ ያስገባል። የመጓጓዣ አገልግሎቶች ገጽታ ተሳፋሪዎችን መሳብ ላይ ወሳኝ ነው፣ ስለዚህ በራይድ ኦን ስም ላይ ውስጣዊ እና ውጫዊ ግምገማ ይካሄዳል። በአጠቃላይ፣ ጥናቱ ከመላው የመጓጓዣ ስርጭት ግቦቻችን ጋር አብረው የሚሄዱ ምክረ ሐሳቦች እና የትግበራ ስትራቴጂዎች ያለው የዕቅድ መዋቅርን ያስቀምጣል።

ለአሁኑ እና ለወደፊቱ የአውቶብስ መጓጓዣ ተሳፋሪዎች የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለማሻሻል እና ለማስፋፋት ብዙ ሥራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ። ይሄ ዕቅድ በመጓጓዣ መንገዶች ደረጃ እና በአገልግሎት ዓይነቶች ጥራቶችን የሚገመግሙ መስፈርቶች እና ግቦችን ያስቀምጣል።

## 1. ፕሮጀክት ማስተዳደር እና ማስተባበር

በአዲስ መልኩ በአውቶብስ ይሳፈሩ ጥናት በ MCDOT የመጓጓዣ አገልግሎቶች፣ የአማካሪ ቡድኑ፣ እና መላው የፕሮጀክት አስተባባሪ ቡድን መካካል የቅርብ ትስስር ይጠይቃል። የ MCDOT የመጓጓዣ አገልግሎቶች ፕሮጀክት አስተዳዳሪዎች እና የአማካሪው ቡድን እና ማንኛውም ወሳኝ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች የሚያካትት፣ ዋና የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን ይኖራሉ።

በተጨማሪም ከሚከተሉት ባለድርሻ አካላት የሚወከሉ የፕሮጀክት አስተባባሪ ቡድኖች ይኖራሉ፦

- MCDOT Division of Transit Services
- MCDOT Director's Office
- Montgomery County Planning Department (M-NCPPC)
- WMATA

ሂደቶችን ለመገምገም፣ በመርሀግብር የተያዙ ተግባራቶችን ለማስተባበር፣ እና የጥናቱን ወሳኝ ደረጃዎች ለማሳካት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ውሳኔዎች እየተወሰኑ እንደሆነ ለማረጋገጥ ዋና የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድኑ በየሳምንቱ ይገናኛል።

ረቂቅ የሚቀርቡ ውጤቶች ላይ ለመወያየት እና ቁልፍ የሆኑ የውሳኔ ነጥቦች ላይ የጋራ መግባባት ለመፍጠር የፕሮጀክት አስተባባሪ ቡዱኑ በየሩብ ዓመቱ ይገናኛል።

## 2. ነባራዊ ሁኔታዎች

ጥናቱ የራይድ ኦን የአሁኑን እና የቅድመ ኮቪድ ሁኔታዎች ላይ ምዘናዎችን ማድረግ ይጨምራል።

<u>በቦታ ላይ የሚመሰረት የውሂብጎታ</u>

ምዘናው የሚከተሉት መረጃዎች ላይ ትንተና ለማድረግ እንዲቻል በቦታ ላይ የተመሰረተ የውሂብጎታ ማዘጋጀትን ይጨምራል፦

1. የአውቶብስ ማቆሚያዎች እና የማቆሚያ ገጽታዎችን ጨምሮ፣ ነባሩን እና ከወረርሽኙ በፊት የነበሩ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ መስመሮችን
2. ለሁለቱም ለቅድመ እና ድህረ ወረርሽኝ ጊዜዎች፣ በራይድ ኦን እና ሜትሮ ባስ ላይ የተደረጉ በአንድ ጉዞ ላይ የተደረጉ የተሳፋሪ መጫኖች እና ማውረዶችን በተመለከተ ከ APC የተገኙ መረጃዎች
3. ለሁለቱም ለቅድመ እና ድህረ ወረርሽኝ ጊዜዎች፣ በራይድ ኦን እና ሜትሮ ባስ ላይ የተደረጉ በአንድ ጉዞ ላይ የተደረጉ መርሀግብርን የመከተል መረጃ (ከመርሀግብር ያፈነገጡ እና በመቆም የጠፉ ጊዜዎች ደቂቃዎችን ቁጥር) ከ AVL/APC የተገኙ መረጃዎች
4. ለሁለቱም ለቅድመ እና ድህረ ወረርሽኝ ጊዜዎች ለራይድ ኦን እና ሜትሮ አውቶብስ የወጡ የ GTFS የመርሀግብር መረጃ እና ለሁለቱም ለቅድመ እና ድህረ ወረርሽኝ ጊዜዎች በቦታ ላይ የተመሰረቱ የሜትሮ መገናኛ መጫኛ እና ማውረጃ መረጃዎች

<u>ትንተና</u>

በቦታ ላይ የተመሰረተው የውሂብጎታ የሚከተሉትን ነባራዊ ሁኔታዎች ላይ ዝርዝር ማብራሪያ ለመስጠት ያገለግላል፦

1. በካውንቲው ወሰኖች ውስጥ እንደዚሁም ልክ እንደ ፕሪንስ ጆርጅስ ካውንቲ፣ ሃዋርድ ካውንቲ እና የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ያሉ በአጎራባች ግዛቶች ላይ የሚገኙ ማቋረጫዎች ላይ የአገልግሎት መስጫ ቦታ እና የትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ መንገዶችን ውህደቶችን መገምገም።

ሀ. የመጓጓዣ ተራ ቦታዎች

ለ. ኢንተርሞዳል ጣቢያዎች-ሁለት ወይም  ከዛ በላይ ማጉዋጉዋዛ መንገዶች

ሐ. ረጅም የትራንስፖርት መንገዶችን

መ. ከፍተኛ የተሳፋሪ ኮሪደሮች/ማቆሚያዎች

2. የአሁኑን አገልግሎቶች ተሳፋሪ መረጃን ከሚከተሉት ማዋቀር:-

ሀ. AVL/APC ውሂብ

ለ. የዳሰሳ ጥናት መረጃ

ሐ. የአፈፃጸም መረጃ

መ. ከአገልግሎት አፈፃጸም ጋር የሚያያዙ የተለያዩ የውሂብጎታ ፋይሎች

3. በ MCDOT በቀረቡትን ነባር መረጃዎች መሰረት፣ የተሳፋሪ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ሁኔታ መገምገም፣ የሚከተሉትን ጨምሮ:-

ሀ. የአውቶብስ ማቆሚያ

ለ. የአውቶብሶች መጠለያ

ሐ. የመጠባበቂያ አግድም ወንበሮች

መ. የአውቶብስ ጣቢያ ቦታዎች

ሠ. መኪና ማቆሚያ እና የተሳፋሪ መጫኛ ቦታዎች

ረ. የአውቶብስ አገልግሎት ሰጪዎች መጸዳጃ ቤቶች

ሰ. የካውንቲውን GIS የእግረኛ መንገዶችን ንጣፍ በመጠቀም ተደራሽነት እና የእግረኛ መንገድ ማግኘት

4. Realtime(የጉዞ ዕቅድ አውጪ)፣CAD/AVL እና Fareboxes ን መገምገም።

ሀ. ልክ እንደ ራይድ ኦን ወደ ሜትሮ ባቡር ዓይነት ብዙ አገልግሎቶችን የሚጨምሩ ጉዞዎችን የሚያካትት የአገልግሎት ሁኔታ፣ አጠቃቀም እና አዋጭነትን መግለጽ።

5. የመነሻ/የመድረሻ ማይል ግንኙነቶችን ጨምሮ የመነሻ-መድረሻ ቅጦችን መገምገም።

ሀ. ከራይድ ኦን እና WMATA እና ፌርቦክስ እና ከስማርትትሪፕ ምንጮች ያሉትን የማስተላለፊያ መረጃዎች መጠቀም

ለ. የመንገድ ሙብራቶችን ወይም ተመሳሳይ የሞባይል ውሂብ ምንጭ በመጠቀም በሁሉም የመጓጓዣ ዓይነቶች ላይ በመላው ካውንቲ ውስጥ የቅድመ ወረርሽኝ እና ድህረ ወረርሽኝ የትራፊክ ፍሰቶችን መገምገም።

6. በኢንዱስትሪው ውስጥ ተመራጭ የሆኑ አሰራሮች ጋር አብሮ እንዲሄድ የሚከተሉትን ደረጃዎች እና ማነጻጸሪያዎችን የሚያካትት ሰንጠረዥ በመጠቀም አጠቃላይ አፈፃጸምን መመዘን (ትግበራ 5 ላይ ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ አቻ ካውንቲዎች ጋር ማነፃጸር):-

ሀ. ብዛት

ለ. ሙሉ ቀን፣ የተጨናነቀ ሰዓት፣ እና ለሊት ላይ የሚሰሩ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ መንገዶችን የሚያካትት የአገልግሎት ፖሊሲ ሽፋን።

ሐ. የመንገዶቹ ምደባ የሚያካትተው:-

- ቋሚ የትራንስፖርት መስጫ መንገዶች
- ቋሚ ተሳፋሪ ማውረጃ ቦታዎች
- ኤክስፕረስ አገልግሎቶች
- የአውቶብስ ብቻ መንገዶች (BRT)
- እንዳስፈላጊነቱ (ፍሌክስ) የሚሰጥ አገልግሎት

መ. በአሁኑ ሰዓት ላይ ያለው ዋጋ ተመን መዋቅር እና ለወደፊቱ የተሰበው የዋጋ ተመን መዋቅር

ሠ. በጊዜ የመድረስ አፈፃጸም እና መርሀግብርን ጠብቆ ደንበኞችን ማስተናገድ

- አጠቃላይ በጊዜ የመድረስ አፈፃፀም
- አማካኝ የመዘግየት ደቂቃዎች
- ወረፋ በመጠበቅ የሚጠፉ ጊዜዎች እና በትራፊክ የተጨናነቁ ኮሪደሮችን ለመለየት አማካኝ ፍጥነት

ረ. የተሰረዙ ጉዞዎች

ሰ. ሙሉ አውቶብሶች - ከመኪናው አቅም በላይ የሚጠቀጠቁ አውቶብሶች።

- የሚቀመጡ ወይም የሚቀመጡ እና የሚቆሙ ሰዎችን የመለያ ወሰኖችን ከግምት ውስጥ ማስገባት
- ከድህረ ኮቪድ የተሳፋሪ መጠን ገደቦች የተለዩ ከሆኑ ማጤን

ሸ. የተሳፋሪ ቅሬታዎች

ቀ. የመኪና የመጫን አቅም ጉዳይ

7. በካውንቲው ወሰኖች ውስጥ የአገልግሎት ሽፋንን መገምገም። ይሄ አገልግሎት ሰጪው ራይድ ኦን ይሁን WMATA የአካባቢውን እና የክልሉን አገልግሎቶች ሙሉ ለሙሉ የመገምገሚያ ዕድል ይፈጥራል። የእነዚህን አገልግሎቶች ላይ የሚተገበሩ ሚናዎች እና ምድቦችን መወሰን።

ሀ. ራይድ ኦን – የአካባቢው አውቶብስ አገልግሎት

ለ. ኤክስትራ –– የተወሰኑ ቦታዎች የሚያቆም አውቶብስ አገልግሎት

ሐ. ፍላሽ – የአውቶብስ ብቻ መንገዶች የሚጠቀም አውቶብስ አገልግሎት

መ. ፍሌክስ - ሲፈለግ ጊዜ አገልግሎት የሚሰጥ

ሠ. WMATA - ሜትሮ አውቶብስ

ረ. MTA/የተሳፋሪ አውቶብስ አገልግሎት

ሰ. የሜሪላንድ ዩንቨርስቲ አውቶብስ

ሸ. ቤተዝዳ ሰርኩሌተር አውቶብስ

ቀ. WMATA ሜትሮ ባቡር (ሽፋን)

በ. ፐርፐል ላይን ባቡር

ተ. WMATA ሜትሮ አክሰስ (3/4- ማይል ሬዲየስ የአገልግሎት ቦታ)

እነዚህ ዝርዝር ሀሳቦች የቴክኒክ ሜሞራንደም ላይ ይገለፃሉ እንዲሁም ያሉትን የራይድ ኦን እና የሜትሮ ባስ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ መንገዶችን አፈፃጸም ላይ በመንገድ ላይ የሚመሰረት መግለጫን በማውጣት ከማጠቃለያ ጋር አብሮ ይቀርባል።

## 3. ግቦች እና ውጤቶች

አሁን ባሉት የአገልግሎት ምዘናዎች ላይ በተገኙት ውጤቶች መሰረት፣ ጥናቱ የአውቶብስ ስርጭት መንገዶችን ግቦች እና የሚጠበቁትን ውጤቶች ያስቀምጣል። ግቦቹ ከ MCDOT የትራንስፖርት አገልግሎት ራዕይ ከሆነው *ማህበረሰቦቻችንን ማገናኘት፣* ከሚለው ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች ጋር አብሮ ይሄዳል። እነዚህ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች፦

- ደህንነት እና ቪዥን ዜሮ
- የአካባቢ እና የአየር ንብረት መካችነት
- የምጣኔ ልማት እና ፍትሃዊ ተደራሽነት

እያንዳንዱ ግብ ከአንድ ወይም ከዚያ በላይ ያሉ ውጤቶች ጋር ይዛመዳል። እነዚህ ውጤቶች የሚለኩ ይሆናሉ በዚህም መሰረት የአራቱ የአውቶብስ ስርጭት አገልግሎት ጽንሰ ሐሳቦች እያንዳንዱን አቅርብዖት ላይ ባላቸው አቅም መሰረት ይወዳደራሉ።

ረቂቅ ግቦቹ እና ውጤቶቹ በቴክኒክ ሜሞራንደሙ ላይ ይቀርባሉ እና በፓወርፖይንት የዝግጅት አቀራረቦች ላይ

በማጠቃለያነት ይቀርባሉ።

## 4. ፖሊሲዎች እና መመሪያዎች

የአገልግሎት መስፈርቶች የአንድ ስኬታማ ውጤት የጀርባ አጥንት ናቸው። የታደሱ ፖሊሲዎች እና የተሻሻሉ መስፈርቶችን ማዘጋጀት ለወደፊቱ የሚወጡ የበጀት እና ለዕቅድ ውሳኔዎች ላይ ለሚገመገሙ አገልግሎቶች መሰረት ይሆናሉ። የአገልግሎት መስፈርቶቹ በተግባር 3 ላይ የተለዩትን ግቦችን ማሳካት እና ውጤቶቹን ማሳየት ላይ አስተዋጽዖ እንዲያደርጉ ተደርገው ይዘጋጃሉ።

1. ስርዓቱ እንዴት እንደሚዋቀር መመሪያ እንዲሆን የአገልግሎት መመሪያዎችን ማደስ፣ ማዘጋጀት እና በግልጽ መተንተን ናቸው። አዲስ መመሪያዎች ሊወጡ ይችላሉ፣ ወይም ፍላሽን፣ ኤክስትራን እና ፍሌክስን ጨምሮ የካውንቲውን የአሁኑን እና ለወደፊቱ ሊሰጡ የሚችሉ የአገልግሎት ጥምረቶችን የሚያካትት ክልላዊ ግብዓት በ WMATA የተዘጋጁ የጎለበቱ የአገልግሎት ምደባዎችን መጠቀም። ሁሉንም የ MCDOT የትራንዚት ዕቅድ እና አገልግሎት ምድቦችን ላይ የተገኙ ግብዓቶችን ጨምሮ፣ የሚከተሉት የአገልግሎት ደረጃዎች ላይ ያሉ መመሪያዎችን መመልከት:-
   ሀ. ከፍተኛ ብዛት
   ለ. ኤክስፐረስ(የፍጥነት)
   ሐ. ሽፋን
   መ. ማይክሮትራንዚት
2. የአውቶብስ መድረሻ ሰዓቶች እና የአገልግሎት ሽፋን ላይ መመሪያዎችን ማውጣት፣ ከዚህ ቀደም የነበሩት የአውቶብስ መድረሻ ሰዓቶች የትኛውም መንገድ ላይ ከ 30 ደቂቃ በላይ አይበልጡም። በዚህ አዲስ ሁኔታ ላይ (ድህረ ኮቪድ) ይሄ ፖሊሲ አሁንም እንደሚሰራና እንደማይሰራ መወሰን።
3. በአንድ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ መንገድ ላይ የስርዓቱን ሽፋን መገምገም። በትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ መንገድ መዋቅር ወይም ስርጭት ሽፋን ላይ ፖሊሲዎችን ማውጣት።
4. ለወደፊቱ የዋጋ ተመን ፖሊሲዎች ላይ ያለውን መዋቅር ማስቀመጥ። ከወረርሽኙ ለማገገም አራት ሊፈጠሩ የሚችሉ ሁኔታዎችን የሚገመግም የተለየ ጥናት እየተከናወነ ይገኛል። ከታች የቀረቡትን ሊፈጠሩ የሚችሉ ሁኔታዎችን እና ውጤቶች የጥናታችን ኢላማ የተደረጉ ገበያዎች ላይ ሊያሳድሩ የሚችሉትን ተጽእኖ መገምገም እና የማሸጋገር ቅናሽ መስጠቶች የሚያሳድሩትን ተጽእኖዎች ግምገማ ማካተት።
   ሀ. በመላው ስርዓት ላይ ዜሮ የዋጋ ተመን
   ለ. በቀን ውስጥ የሆነ ሰዓት ላይ ዜሮ የዋጋ ተመን ማውጣት
   ሐ. የተቀነሱ የዋጋ ተመኖች ($1)
   መ. ለዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ማህበረሰቦች ነፃ የዋጋ ተመን ወይም ቅናሽ መስጠት (በገቢ ላይ የሚመሰረት ጽንሰ ሐሳብ)
5. እያንዳንዱ የአውቶብስ ማቆሚያዎች ላይ ባሉት ምድቦች መሰረት ሊቀርቡ የሚችሉ የተቋም ገጽታዎችን ደረጃ ላይ መመሪያዎችን ማውጣት።

ረቂቅ የአገልግሎት መስፈርቶቹ በቴክኒክ ሜሞራንደሙ ላይ ይቀርባሉ እና በፓወርፖይንት የዝግጅት አቀራረቦች ላይ በማጠቃለያነት ይቀርባሉ።

## 5. የአውቶብስ ስርጭት ምዘና

ከጊዜ ወዲህ፣ የአገልግሎት መስፋፋቶች እና ፍላጎት፣ የሥነ ሕዝብ ፍላጎቶች እና የመልሶ ልማት ስራዎችን ያገናዘቡ አዲስ የትራስፖርት አገልግሎት መስጫ መንገዶች ነበሩ። የዚህ ጥናት አብዛኛው ክፍል የሚያተኩረው በተለያዩ መነጽሮች አገልግሎቶቹን መቃኘት ነው። እነዚህ ዋነኛ የትኩረት ቦታዎች የሚያካትቱት:-

***የአቻ ግምገማ***

1. በተግባር 3 ላይ እንደተለዩት እና የሚከተሉትን ምክንያቶች መሰረት ተመሳሳይ የሆኑ ግቦች ማሳካት ላይ አሁን የሚያደርጉት ጥረቶች መሰረት እስከ አራት የሚደርሱ የሚያነቃቁ የአውቶብስ ትራንስፖርት መስጫ መንገዶችን ዋና የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድኑ ይመርጣል።

   ሀ. አገልግሎት የሚሰጥበት ቦታ መጠን

   ለ. አገልግሎት የሚሰጥበት ቦታ ሕዝብ ቁጥር

   ሐ. የስርጭት መንገዶች ማይሎች

   መ. ዓመታዊ የአገልግሎት ማይሎች

   ሠ. ዓመታዊ የአገልግሎት ሰዓቶች

   ረ. ዓመታዊ ተሳፋሪነት እና የተሳፋሪ ማይሎች

   ሰ. የተለያዩ አገልግሎቶች ቅይጥ

   ሸ. የተሸከርካሪው መኪና ሰው የመያዝ አቅም እና የመኪናው ዓይነት

   ቀ. የገንዘብ መዋቅር

   በ. የአስተዳደር መዋቅር

2. አሁን ያለውን የሞንትጎመሪ ካውንቲ የአውቶብስ ስርጭት ከብሔራዊ ትራንዚት የመረጃ ውሂብጎታ ላይ በተገኙ መረጃዎች መሰረት ከአቻ ተምሳሌት ከሚሆኑ ካውንቲዎች ጋር ንጽጽር ይደረጋል። እንደ መነሻ ጥናት፣ MCDOT በሜሪላንድ በዓመቱ ሶስት ጊዜ በሚካሄደው የግምገማ ሂደት መሰረት አቻ የትራንዚት ኤጀንሲዎችን ለመለየት የሚያገለግለውን መረጃ ያቀርባል።

3. ዋና የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድኑ ልክ እንደ የአገልግሎት ፖሊሲዎች፣ ያገለገሉ ቴክኖሎጂዎች፣ እና የአያያዝ መስፈርቶች ዓይነት ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት ከአቻ ተምሳሌት ካውንቲዎች ጋር የሚጠቀሙበት መጠይቅ ያዘጋጃሉ።

4. በተግባር 2 ውስጥ እንደተቀመጠው የነባሮቹ ስርጭቶች ውጤቶች ለአራት ተምሳሌት የሚሆኑ አቻ ካውንቲዎች ጋር ሲነፃጸር ነው፡-

   ሀ. ብዛት

   ለ. ሙሉ ቀን፣ የተጨናነቀ ሰዓት፣ እና ለሊት ላይ የሚሰሩ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ መንገዶችን የሚያካትት የአገልግሎት ፖሊሲ ሽፋን

   ሐ. የመንገዶቹ ምደባ የሚያካትተው፡-

   - ቋሚ የትራንስፖርት መስጫ መንገዶች
   - ቋሚ የተሳፋሪ ማውረጃ ቦታዎች
   - ኤክስፕረስ አገልግሎቶች
   - የአውቶብስ ብቻ መንገዶች (BRT)
   - እንዳስፈላጊነቱ የሚሰጥ አገልግሎት

   መ. የዋጋ ተመን መዋቅር

   ሠ. በጊዜ የመድረስ አፈፃጸም እና መርሀግብን ጠብቆ ደንበኞችን ማስተናገድ

   - አጠቃላይ በጊዜ የመድረስ አፈፃፀም
   - አማካኝ የመዘግየት ደቂቃዎች
   - ወረፋ በመጠበቅ የሚጠፉ ጊዜዎች እና በትራፊክ የተጨናነቁ ኮሪደሮችን ለመለየት አማካኝ ፍጥነት

   ሰ. የተሰረዙ ጉዞዎች

   ሸ. ሙሉ አውቶብሶች - ከመኪናው አቅም በላይ የሚጠቀጠቁ አውቶብሶች።

- የሚቀመጡ ወይም የሚቀመጡ እና የሚቆሙ ሰዎችን የመለያ ወሰኖችን ከግምት ውስጥ ማስገባት
- ከድህረ ኮቪድ የተሳፋሪ መጠን ገደቦች የተለዩ ከሆኑ ማጤን

ቀ. የተሳፋሪዎች የቅሬታ ምጥን
በ. የመኪና የመጫን አቅም ጉዳይ
ተ. የማቆሚያ ቦታዎች ገጽታዎች እና ተደራሽነት

5. አማካሪው የአቻዎች ግምገማ ቴክኒካል ሚሞራንደም ያዘጋጃል።

**<u>የገበያ ጥናት</u>**

1. ለራይድ ኦን እና ሜትሮ አውቶብስ አገልግሎቶች የጉዞ ቅጦች የመነሻ እና የመዳረሻ (O/D) ትንተና ማዘጋጀት።
2. ሊሆን የሚችለውን የመጓጓዣ አጠቃቀም የትራንስፖርት ቅርበት ማውጫ (Transit Propensity Index) (TPI) መለየት።
3. በአገልግሎት መስጫው ቦታ ላይ የትራፊክ ትንተና ዞን (Traffic Analysis Zone) (TAZ) መገምገም።
4. የአሁኑ መዋቅር እያደገ እና እየተስፋፋ የመጣውን የማህበረሰባችንን ፍላጎት የሚያሟላ መሆኑን ለማረጋገጥ አጠቃላይ የስርዓት ንድፍ ግምገማ ማድረግ።

   ሀ. ብዙ ሕዝብ ያላቸው አገልግሎት ያላገኙ ቦታዎች (መጓጓዣ አልባ ቦታዎች)

   ለ. ያለ ተደጋጋሚ ወይም መደበኛ አገልግሎት በትራፊክ የሚጨናነቁ መዳረሻ ቦታዎች

   ሐ. በተለይ ልክ እንደ የሕክምና ቀጠሮዎች የመሳሰሉ፣ ወሳኝ አገልግሎቶችን ለማግኘት በአሁኑ ሰዓት ያሉ መሰናክሎችን መለየት

5. የአሁኑን መዋቅር እና እንዴት የተለያዩ አገልግሎቶች ከአውቶብስ ብቻ መንገድ ትራንስፖርት (BRT) ጋር ሊዋሀዱ እንደሚችሉ መገምገም።

   ሀ. ለአካባቢው የአውቶብስ አገልግሎት (ለሁለቱም ራይድ ኦን እና ሜትሮባስ) እና የአውቶብስ ብቻ መንገድ ትራንስፖርት (BRT) አገልግሎቶች የስርዓት ንድፍ ይወስኑ።

6. ከዚህ ቀደም የተከናወኑ የዳሰሳ ጥናቶችን መገምገም።
7. የአገልግሎት መስጫ ቦታው ላይ የአካባቢውን የጉዞ ፈጣሪዎችን እና መገናኛ ቦታዎችን መገምገም።

   ሀ. ከፍተኛ የትምህርት ተቋዋማት

   ለ. ትምህርት ቤቶች

   ሐ. የመዝናኛ ማዕከላት

   መ. ቤተ መፃሕፍቶች

   ሠ. ዋና ፓርኮች

   ረ. የቅጥር ማዕከላት

   ሰ. የቢሮ ግንባታዎች

   ሸ. ሆስፒታል እና ሕክምና መስጫ ማዕከላት

   ቀ. ባህላዊ እና ለትርፍ ያልተቋቋሙ አገልግሎቶች

   በ. የሸቀጥ መደብሮች

8. የገበያ ትንተናው በተግባር 2 ላይ የተዘጋጁትን የቦታ የውሂብጎታዎችን ይገነባል እና ማንኛውም የአገልግሎት ክፍተቶችን ይለያል። ውጤቶቹ የማሳያ ካርታዎች እና የፓውርፖይንት ዝቅጅት አቀራረብ ማጠቃለያን ጨምሮ የቴክኒክ ሜሞራንደም ላይ ይቀርባሉ።

**የመሬት አጠቃቀም/ልማት/የትራንስፖርት ዕቅዶች**

ባለፉት ብዙ ዓመታት ውስጥ የተለያዩ ጥናቶች ተከናውነዋል፣ የራይድ ኦን በአዲስ መልክ ጥናት ከካውንቲው አጠቃላይ ዕቅዶች ጋር አብሮ እንደሚሄድ ለማረጋገጥ ከዚህ ቀደም የነበሩ ጥናቶችን መገምገም አስፈላጊ ነው። የሚከተሉት ዕቅዶች ግምገማዎቹ ላይ መካተት አለባቸው፡-

1. ቤተዝዳ የትራንዚት መንገድ
2. የአውቶብስ ስርጭት አስተዳደር ዕቅድ
3. በመላው ካውንቲ ውስጥ የሚገኙ የትራንዚት ኮሪደሮች የትግበራ ዋና ዕቅድ እና ተያያዥ የአውቶብስ ብቻ መንገድ ትራንስፖርት ጥናቶች
4. WMATA የአውቶብስ ሽግግር ጥናት
5. ኮሪደር ከተማዎች የትራንዚት መንገዶች
6. I-495/I-270 የሚተዳደሩ መንገዶች ጥናት
7. MTA ፐርፕል ላይን
8. የጋራ መንገዶች/የብስክሌት መንገዶች መርሀግብር
    ሀ. የተጋራውን መንገዶች መርሀግብር መገምገም እና በድጋሚ ማየት ተቀያያሪ የአውቶብስ ቦታ ማቆሚያዎች እና የእግረኛ መዳረሻ ፕሮቶኮልን መወሰን።
    ለ. ለአውቶብስ ብቻ ቅድሚያ መንገዶች ቅድመ ሙከራ እየተከናወነባቸው ያሉ ቦታዎችን መገምገም እና ተጨማሪ ቦታዎች የትራንዚት ምልክት ቅድሚያ መስጠት፣ አውቶብሶች ወረፋ እንዳይጠብቁ የሚያስችሉ ዘዴዎችን መምከር እና የአውቶብስ አውታረመረብ ላይ ያሉትን ተጽእኖዎች ማካተት።
    ሐ. የአውቶብስ መንገዶች ከጥራት እና አስተማማኝነት አንፃር አጠቃላይ ስርዓቱን ማሻሻል ላይ ከፍተኛ የሆነ ተጽእኖ እንደሚፈጥሩ መፈተሽ።
9. ትራይቭ 2050
10. ሞንትጎመሪ ካውንቲ የአየርንብረት የድርጊት መርሀግብር
11. ቪዥን ዜሮ
12. ግሬት ሴኔካ ሳይንስ ኮሪደር (GSSC) ትራንዚት አውታረመረብ
13. መንገዶች የማየት አካላስንክልና ላለባቸው ሰዎች  አስተማማኝ እና ይበልጥ ተደራሽነት እንዲኖራቸው ማቀድ እና ንድፍ ማውጣት
14. የበላይ ዕቅዶች
    ሀ. የቦታ የበላይ ዕቅዶች
    ለ. ሴክተር ዕቅዶች
    ሐ. የትግበራ የበላይ ዕቅዶች
15. ኮሪደር ፎርዋርድ
16. ለተለያዩ የትራንዚት ማዕከሎች የተቋም ዕቅድ ጥናቶች

አማካሪው ከዚህ ቀደም የወጡትን ዕቅዶች እና ጥናቶች እና ለራይድ ኦን በአዲስ መልክ ጥናት ቁልፍ የሚሆኑ ግብዓቶችን በመለየት የማጠቃለያ የቴክኒክ ሜሞራንደሞችን ያዘጋጃል።

**መሰረተልማት**

የትራንስፖርት ማውረጃ እና መጫኛ ቦታዎች ገጽታዎች የፈጠራ ቴክኖሎጂ እና መዋዕለ ነዋዮች በመጠቀም አዲስ ተሳፋሪዎችን ለመሳብ እና ያሉትን ለማቆየት ዕድሉን ይፈጥራሉ።  የእነዚህን መርሀግብሮች ተግባራዊነት መረዳት አስፈላጊ ነው።

1. የአውቶብስ ጋራጆች

   *ሀ. ዕቅዱን ይበልጥ ለማገዝ የአሁኑን የአውቶብስ ጋራጆችን እና የሚሞከሩ የመስፋፋያ ስትራቴጂዎችን መገምገም።*

   *ለ. የዜሮ ብክለት ተሽከርካሪዎች መኖርን ለመደገፍ እያንዳንዱን የአሁኑን ጋራጆች ፍላጎት መለየት እና በሽግግሩ ወቅት ሁለቱንም የሚዘወተሩ አውቶብሶች እና ዜሮ-ብክለት አውቶብሶችን ለመደገፍ ማንኛውም ነባር ጋራጆችን አዋጭነት እንዳላቸው መለየት።*

2. የተሳፋሪ ተቋማት

   *ጥናቱ የአሁኑን የአውቶብስ ተሳፋሪ ተቁማትን ፖርትፎሊዮ፣ የማውረጃ እና መጫኛ ቦታዎች እና ጣቢያዎችን የመመደቢያ ስርዓት ማዘጋጀት ይገመግማል። የምደባ ዓይነቶች የሚመሰረቱት አገልግሎት የተሰጣቸው ተሳፋሪዎች አማካኝ ከፍተኛ ቁጥር፣ የማውረጃና መጫኛ/ጣቢያው የሚያገለግሉ የትራንዚት ዓይነቶች፣ እና የማውረጃና መጫኛ/ጣቢያው የሚያገለግሉ የትራንዚት መንገዶች/ጣቢያዎች ብዛት። እያንዳንዱ የምደባ ዓይነት የሚመከሩትን የተለያዩ የተሳፋሪ መጫኛና ማውረጃ ቦታዎችን ገጽታ፣ በቀጥታ ከሚሰራጭ ጊዜ መረጃ ጋር ከአውቶብስ ማቆሚያ እስከ መጠለያ ድረስ ያካትታል። ይሄ የምደባ ስርዓት የተለየ ፕሮጀክት በመንደፍ ሊዘጋጅ የሚችል የትራንዚት ንድፍ መመሪያ ላይ እንደ መነሻ ሐሳብ ሊያገለግል ይችላል።*

   *የማውረጃና መጫኛ/ጣቢያው ምደባ ስርዓት ማዘጋጀት ላይ፣ ጥናቱ የሚከተሉትን ከግምት ውስጥ ያስገባል እንደዚሁም ያካትታል፡-*

   *ሀ. የአውቶብስ ማቆሚያ እና የአውቶብስ መጠለያ መርሀግብርን እንዲያካትቱ የተሳፋሪ ተቋማትን አጠቃላይ መርሀግብር ይገምግሙ።*

   *ለ. በመላው የተለያዩ አገልግሎቶች ሂደት ምዘና ላይ የአውቶብስ ማቆሚያ መለያ ኮዶችን እና ስያሜዎችን መረዳትን ማሳደግ እና ማጎልበት።*

   *ሐ. መረጃ የማግኛ ተመራጭ አሰራሮችን ለመገምገም እና ለመወሰን እንደዚሁም ጊዜውን የጠበቀ የአውቶብስ ማቆሚያ ምልክቶች እና የአውቶብስ መጠለያዎችን መገምገም እና መለየት።*

   *መ. የአውቶብስ ማቆሚያ ቦታዎችን፣ የአውቶብስ ጣቢያዎችን፣ መደገፊያዎች እና የአውቶብስ ሠራተኞች መጸዳኛ ቤቶችን አጠባበቅ መገምገም።*

   *ሠ. ለፓርክ እና ራይድ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች አሁን ያለውን ስምምነት መገምገም።*

   - *ያሉት የመኪና ማቆሚያዎች ቁጥር*
   - *የመኪና ማቆሚያ ባለቤትነት*
   - *የመኪና ማቆሚያ ወጪ*
   - *የነዋሪ/ወርሃዊ ቦታዎች*
   - *አጠቃቀም*
   - *የትራንዚት አውቶብስ መዳረስ እና ስርጭት*

   *ለ. ለ BRT አአልግሎቶች የተገነቡ የአሁኑን የትራንዚት ማዕከሎች እና የትራንዚት ጣቢያኦች ተግባራቶችን ይወስኑ፡-*

   - *እነዚህን የትራንዚት ማዕከሎች ለመወሰን በአሁኑ ሰዓት የሚያገለግሉትን የተለያዩ መሪሃ ቃላቶችን ማጤን። እነዚህ ከሜትሮ ባቡር ጣቢያዎች ጋር የማይዛመድ ቦታዎች ናቸው እና ለሽግግር ቢያንስ ሶስት ወይም ተጨማሪ መንገዶች የሚገናኙባቸው ቦታዎች ናቸው።*
   - ጀርመንታውን መናኸርያ ማዕከል
   - ሌክፎረስት መናኸርያ ማዕከል
   - ማይልስቶን መናኸርያ ማዕከል
   - ትራቪሊ መናኸርያ ማዕከል
   - ዌስትፊልድ ሞንትጎመሪ ሞል መናኸርያ ማዕከል

- ቦይድስ መናኸርያ ማዕከል
- ዋይት ኦክ መናኸርያ ማዕከል

ሐ. ለአውቶብስ ማቆሚያ ቦታዎች እንደዚሁም ለእግረኛ መንገዶች መዳረሻ እና ማቋረጫ መንገዶች መመሪያዎችን መገምገም እና ማዘጋጀት

- የቅርብ እና ይርቀት የአውቶብስ ማቆሚያ ቦታዎችን በተመለከተ ደረጃዎችን የማውጣት አስፈላጊነት መቃኘት
- የእንቅስቃሴ አካለ ስንክላን (ADA) ለሆኑ ተሳፋሪዎች የመዳረሻ ደረጃዎችን ማውጣት

መ. የአቅጣጫ መጠቆሚያዎች ላይ እገዛ የሚሰጡ የአውቶብስ ማቆሚያ ቦታዎችን መናገር ላይ የተሻሉ አሰራሮችን መገምገም እና ጥቆማ መስጠት

ሠ. የአውቶብስ መጠለያዎችን ምስል ማሳያ/ ጊዜውን የጠበቁ መረጃዎችን በሚሰጡ መረጃዎች ን በመጠቀም መገምገም እና ያሉትን ግብዓቶች እና መተግበሪያዎች የሚጠቀሙ ሁሉንም የአውቶብስ ማቆሚያ ቦታዎች ላይ ቆጥራ ማከናወን።

- የአውቶብስ ማቆሚያ/የመጠለያ ቆጠራ ጥናት
- የአውቶብስ ማቆሚያ የውሂብጎታ

ረ. የአውቶብስ ማቆሚያዎች ላይ ለብስክሌት ተደራሽነት ማሻሻያዎች ላይ መመሪያዎችን መገምገም እና ማዘጋጀት።

የጋራጆች እና የተሳፋሪ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ላይ የሚደረገው የመሰረተ ልማት ግኝቶች የቴክኒክ ሚሞራንደሙ ላይ ይቀርባሉ እና በፓወርፖይንት የዝግጅት አቀራረብ ላይ በማጠቃለያ መልኩ ይቀርባሉ።

**ቴክኖሎጂ**

በ MCDOT ትራንዚት ክፍል ውስጥ እየተካሄዱ ያሉ ብዙ የቴክኖሎጂ ኢንሼቲቮች አሉ፣ እና የተለያዩ ፕሮጀክቶችን እና ተግባራዊነቶችን ለመረዳት አስፈላጊ ይሆናል። ጊዜ ያለፈባቸውን ስርዓቶች ማሻሻል፣ የአየርንብረት ለውጥ፣ የዘር እኩልነት እና የደንበኛ መረጃ የካውቲው ዋነኛ ቅድሚያ የሚሰጣቸው መረጃዎች ናቸው።

1. አዲሱን የ CAD/AVL ስርዓት (ክሌቨር ዲቫይስ) እና በስርዓቱ ውስጥ ያሉትን ተግባራዊነቶች መገምገም።
   ሀ. APC ውሂብ
   ለ. ራይድቼክ ፕላስ
2. ዜሮ ብክለት ያላቸው አውቶብሶች፣ ለምሳሌ፣ የኤሌትሪክ፣ ባትሪ ኤሌትሪክ አውቶብሶች እና ሃይድሮጅን ነዳጅ ሴል አውቶብሶች የመሳሰሉት ላይ ለመሸጋገር ዕቅድ መጠቆም
3. መንገዶች የኤሌትሪክ መኪናዎችን የማስተናገድ አቅም እና መሰረተ ልማቶች እንደዚህም በስራ ላይ እያሉ ከባትሪ መሙያ ጣቢያዎች ጋር የሚነጋገሩ ቴክኖሎጂ እንዲኖራቸው ዕቅድ ማውጣት።
4. ዜሮ ብክለቶችን የሚያስከትሉ አውቶብሶች ላይ ለመሸጋገር እና ለኤሌትሪክ ኀይል ማመንጫዎች መመሪያዎችን መስጠት ላይ ያሉትን የጊዜ ሰሌዳዎችን መገምገም።
5. የ BRT ጣቢያዎች ላይ ከቦርድ ውጪ የሚደረጉ ክፍያዎችን የመሰብሰብ አሰራሮችን መገምገም እና ለስርጭቱ ያላቸውን ምርታማነት እና ጥቅሞች ላይ ትንተና መስጠት።
6. ጊዜውን የጠበቀ መረጃ  የመስጠት አቋምን መገምገም።
7. ጊዜውን ለጠበቀ መረጃ አተገባበር እና ለተጠቃሚዎች ያለውን ተደራሽነት ላይ ያሉ ምርጥ አሰራሮችን መፈተሽ።
8. የመኪና አውቶሜሽንን መዳሰስ።
9. ተፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶችን ማስፋፋትን መፈተሽ ለምሳሌ ፍሌክስ ወይም አሊስ።

የጋራጆች እና የተሳፋሪ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ላይ የሚደረገው የቴክኖሎጂ ግኝቶች የቴክኒክ ሚሞራንደሙ ላይ

ይቀርባሉ እና በፓወርፖይንት የዝግጅት አቀራረብ ላይ በማጠቃለያ መልኩ ይቀርባሉ።

**<u>ከንውኖች/ስምሪቶች</u>**

ዕቅድን የመተግበሪያ ወሳኝ አካላትች አገልግሎቱ እንዴት እንደሚሰጥ መወሰን ነው። የስምሪት መሰረተ ልማቶችን መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው።

1. የዲፖ መዋቅር፣ የስምሪት ወጪቆጣቢነት እና የዕድገት ስትራቴጂዎች፣ በተለይ ወደ ዜሮ ብክለቶች ላይ የሚደረገው እንቅስቃሴን ከግምት በማስገባት መፈተሽ እና ጥቆማ መስጠት።
2. መደበኛ የአሰራር ቅደም ተከተሎችን መገምገም እና በኢንዱስትሪው ውስጥ ካሉ ምርጥ አሰራሮች ጋር ማወዳደር።
3. ለዘር እኩልነት የስምሪት ዓይነት እና የሚሰጡትን አገልግሎቶች መፈተሽ።
4. የአሰራር ተዋረዱን ተግባራዊነት መፈተሽ እና በኢንድስትሪው ውስጥ ካሉ ምርጥ አሰራሮች ጋር ማወዳደር።
5. የራይድ ኦን ደህንነት እና የስልጠና መርሀግብርን ለመፈተሽ ዕቅድ እየወጣ ነው። ሂደቱን መረዳት እና ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ ጊዜ ዕቅዶቹን መገምገም አስፈላጊ ነው። ሂደቱን እና በኢንዱስትሪው ውስጥ ያሉ ምርጥ አሰራሮችን መዳሰስ የዕቅዱ አካል መሆን አለባቸው።
6. ጥናት እና የኢንዱስትሪውን ምርጥ አሰራሮች እንደ መመሪያ በመውሰድ የአውቶብስ ሠራተኞችን መሳብ እና እንዲቆዩ ለማድረግ አዲስ የፈጠራ ስትራቲጂዎችን መጠቀም እና ማመላከት። በአሁኑ ሰዓት ካሉት የራይድ ኦን ሠራተኞች የአስራር መሻሻያዎች እና ሠራተኞችን ማቆየት ላይ መረጃ ግብረመልስ ማግኘት።

የከዋኞች እና የስምሪት ላይ የሚገኘው መረጃ ግኝቶች የቴክኒክ ሚሞራንደሙ ላይ እና በፓወርፖይንት የዝግጅት አቀራረብ ላይ በማጠቃለያ መልኩ ይቀርባሉ።

***<u>የገበያ መምሪያ</u>***

የተሳፈሪዎችን ቁጥር እና ግንዛቤ የማሳደጊያ ሌላኛው ወሳኝ የሆነው አካል ግልጽ እና አጠር ያሉ መልዕክቶች ናቸው።

1. አሁን ያለውን አመለካከት (በትራዚት ላይ የኮቪድ ደህንነት አጠባበቅ) መፈተሽ እና በአዲስ መልኩ ስም የማውጣት አማራጮች እና መመሪያዎችን መጠቀም።
2. ርእስ አምስት እና የተወሰነ የእንግሊዘኛ ዕውቀት ብቃቶችን ከግምት ባስገባ መልኩ አሁን ያሉትን የማስታወቂያ ምልክቶች ከፍተኛ ግንዛቤ እንዲፈጥሩ መፈተሽ።
   ሀ. የመንገድ መጠቆሚያ ምልክቶች
   ለ. የውጭ መግባባቶች የሚያካትቱት የአውቶብስ ማቆሚያ ምልክቶችን ነው።
3. ካርታዎችን እና የጊዜ ሰሌዳዎችን መገምገም እና ለተጨማሪ ማሻሻያ ጥቆማዎችን በማቅረብ ከአቻ ቡድኖች ጋር ማወዳደር።
4. የአፈፃጸም መለኪያዎች፣ የክፍያ ተመኖች፣ መንገዶች፣ መርሀግብሮች፣ ማህበራዊ ሚዲያ፣ እና አጠቃላይ መግባባቶች ጋር የሚያያዙ ተያያዥ መረጃዎችን በትራንዚት ዲቪዥን ድረገጽ ላይ መገምገም።
5. የመረጃ ተደራሽነት ጋር በተያያዘ የአሁኑን አሰራር መፈተሽ።

የገበያ ጥናት ላይ የሚገኘው መረጃ ግኝቶች የቴክኒክ ሚሞራንደሙ ላይ እና በፓወርፖይንት የዝግጅት አቀራረብ ላይ በማጠቃለያ መልኩ ይቀርባሉ።

## 6. የባለድርሻ አካላት

በመላው ጥናት ላይ ከባለድርሻ አካላትን ራዕይ እና ግብረመልሶችን መሰብሰብ አስፈላጊ ነው። እነዚህ የባለድርሻ አካላት መመሪያ እና መዋቅር ለማግኘት የመጀመሪያው ደረጃ ላይ ይካተታሉ። የፕሮጀክቱ የተለያዩ መድረኮች ላይ ቀጣይነት ያለው ጊዜያዊ መረጃ ማግኘት ያስፈልጋል። ይሄ ዝርዝር ምዳሜ ላይ የሚያደርስ አይደለም፣ እና ሌሎች ሊካተቱበት ይችላሉ።

1. ኤክስኪዩቲቭ ብራንች ኤጀንሲዎች
2. ካውንቲ ካውንስል
3. ሜሪላንድ-ብሔራዊ ካፒታል ፓርክ እና የዕቅድ ኮሚሽን (MNCPPC)
4. የአካባቢው የከተማ መስተዳደሮች
5. የአውቶብስ ሠራተኞች/ትኬት ቆራጮች/MCGEO
6. WMATA - ሜትሮ አውቶብስ
7. የትራንዚት ተሟጋች ቡድኖች
8. ሜትሮፖሊቲያን ዋሽንግተን የመንግስት ካውንስል (MWCOG)
9. መሪላንድ የትራንስፖርት መምሪያ (SHA/MTA)
10. MCDOT የተሳፋሪ አገልግሎቶች/TDM
11. ሞንትጎመሪ ካውንቲ ቻምበር ኦፍ ኮሜርስ
12. የሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች
13. የካውንቲው እና የግዛቱ የጤና እና የሰብዓዊ አገልግሎቶች ኤጀንሲዎች
14. ሆስፒታሎች እና ሕክምና መስጫ ማዕከላት
15. የቤቶች ዕድል ኮሚሽን
16. የመኖሪያ ሰፈሮች እና የቤት ባለቤቶች ማህበራት
17. ሞንትጎመሪ ካውንቲ የአካላስንኩላን ሰዎች ኮሚሽን
18. ዋሽንግተን ሰብአርባን ትራንዚት ኮሚሽን
19. ሞንትጎመሪ ካውንቲ ዕድሚያቸው የገፉ ሰዎች ኮሚሽን

## 7. የሕዝብ ተሳትፎ

ግልጽነት የጥናቱ መሳካት ላይ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ከባለድርሻ አካላት ጋር ግልጽ የሆነ ውይይት ማድረግ ወጥ የሚሆን ከሆነ የሕዝብ ተሳትፎ (ሁለቱም በኢንተርኔት እና በአካል በመገናኘት የሚደረጉት) ሂደት እንደሚኖር ግልጽ ነው።

1. ለትብብር ውይይቶች የሚያነሳሳ የሕዝብ ተሳትፎ ዕቅድ ማውጣት። ዕቅዱ በራይድ ኦን በአዲስ መልክ ጥናት ላይ ቁልፍ የማዕዘን ድንጋዮችን ለመለየት እና እያንዳንዱ የማዕዘን ድንጋይ ላይ ተገቢውን የሕዝብ ተሳፎን መለየት ያስፈልጋል።
2. በፕሮጀክቱ ድርጣቢያ፣ ማህበራዊ ሚዲያ፣ ደንበኞች በመንገድ ላይ ተሳፍረው ሳለ እና በክፍት ቤት ውስጥ በሚገኙበት ሰዓት ለማግኘት በኢንተርኔት የሚደረጉ ስብሰባዎች በኩል ለመገናኘት መሰረታዊ ቅድመ ሁኔታዎችን ማመቻቸት።
3. የደንበኛ እርካታ የዳሰሳ ጥናት በማከናወን የአሁኑን ተጠቃሚዎች አማራጮች መገምገም።
4. የአውቶብስ ስርጭት ያለባቸው መገናኛ ቦታዎችን (ለምሳሌ፣ ሲልቨር ስፕሪንግ፣ ሮክቪል፣ ጀርመንታውን) ማዕከል ያደረጉ መልክዓ ምድራዊ ንዑስ ቦታዎች መሰረት የትኩረት ቡድንን መፍጠር። የትኩረት ቡድኑ አጠቃላይ ቁጥር ከስምንት መብለጥ የለባቸውም፣ ለእያንዳንዱ ቡድን ደግሞ ሁለት ስብሰባዎች እንዲደረጉ ታቅዷል። የመጨረሻ ስምንት ቡድኖች እንዲኖሩ ለማድረግ፣ በንጽጽር ተቀራራቢ መልክዓ ምድራዊ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ቦታዎች በአንድ ላይ ሊቦደኑ ይችላሉ(ለምሳሌ ጀርመንታውን እና ክላርክስበርግ) የእያንዳንዱ የትኩረት ቡድን የመጀመሪያ ስብሰባ የራይድ ኦን በአዲስ መልክ ግቦችን መገምገምን ያካትታሉ እና "ክፍተቶቹን ያገናኙ" የሚለው ልምምድ ላይ የሚሳተፈው ቡድን አሁን ባለው ተሳፋሪ፣ የተለዩ የእንቅስቃሴ ማዕከሎች፣ እና የወደፊት ዕድገት ላይ ያሉ ጠቃሚ መረጃዎችን በመጠቀም ሊሆኑ የሚችሉ የአውቶብስ መንገዶች ላይ አስተያየታቸውን ይሰጣሉ። የእያንዳንዱ የትኩረት ቡድን ሁለተኛ ስብሰባ የመጀመሪያው ስብሰባ ላይ በስነ

ሐሳብ ደረጃ ያሉ የአውቶብስ መንገዶችን እንዴት እውን ሊሆኑ እንደሚችሉ ክትትል በማድረግ ይጀምራል እና በንዑስ አካባቢው ላይ ባሉ የአውቶብሶች ቁጥር መሰረት ለእያንዳንዱ መንገድ ሊሆኑ የሚችሉ መንገዶች ላይ አስተያየታቸውን ይሰጣሉ።

5. ከተለያዩ ተሚጋች ብድኖች፣ ሲቪክ ማህበረሰባት፣ የማህበረሰብ ቡድኖች ወዘተ ጋር የሕዝብ ስብሰባዎችን ማድረግ።
6. የጥናቱ መላው ሂደት ላይ የፕሮጀክቱ ቡድን ይሳተፋል። ስለዚህ፣ የተቀመጡት የሚሰሩት ስራዎች የሂደቱ መጀመሪያ ላይ ይወሰናሉ።
7. በቃል እና በጽሁፍ የሚደረጉ የቋንቋ እገዛዎች ጋር በማጣመር ለአገልግሎቶቹ ስሜት የሚሰጡ ተደራሽነት ያላቸው በራሪ ጽሁፎችን ማዘጋጀት። በአጠቃላይ ከሚገመገመው የሕዝብ ቁጥር ውስጥ 5% ወይም 1000 ሰዎች ከሆኑ፣ ወይም ደግሞ ከሁለቱ ያነሰውን በመምረጥ፣ ሁሉም ብቁ የሚሆኑ ቋንቋዎች ላይ የትርጉም አገልግሎቶች ይቀርባሉ። ትርጉሞቹ ስፓኒሽኛ፣ ማንዳሪን፣ አማርኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ሩሲያኛ፣ እና ቬትናምኛ ያካትታሉ ተብለው ይጠበቃሉ። የእነዚህ መጣጥፎች ምሳሌ የሚያካትቱት፡-
    ሀ. ካርታዎች
    ለ. የሚዲያ ማስታወቂያዎች
    ሐ. የስርጭት ማስታወቂያ
    መ. የፕሮጀክት ድረጣቢያ
    ሠ. የስብሰባ አጀንዳዎች
    ረ. ፓወርፖይንት የዝግጅት አቀራረቦች
    ሰ. የማሳያ ቦርዶች
    ሸ. የተለያዩ ታዳሚዎችን የሚስቡ እና በግልጽ መልዕክት የሚያስተላልፉ ኢጋዥ ምስሎች
5. ለሁሉም ተሳትፎዎች እና መገኛቶች የስብሰባ ሚኒት ማዘጋጀት።

## 8. የአገልግሎት ጽንሰ ሐሳቦች እና ጠቃሚ ምክሮች

የዚህን ጥናት የተለያዩ ክፍሎች መገምገም አዲስ አገልግሎት ንድፎች እና አማራጮች ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ ነገሮችን ለማየት መንደርደሪያ ይሆናሉ። እያንዳንዱ ተግባር የጽንሰ ሐሳብ ዕቅድ የማግኘት አላማ በማስቀመጥ ይገለፃል። ተግባራቶቹ በዚህ ጥናት ላይ ለመድረስ ያስቻሉ መረጃዎችን መነሻ ያደርጋሉ። ሁሉን አቀፍ የሆነው አሰራር የገበያ ትንታኔ፣ የመሬት አጠቃቀም ልማት፣ መሰረተ ልማት፣ ቴክኖሎጂ፣ ስምሪቶች፣ ገበያ፣ እና የሕዝብ ተሳትፎ ማካተት አለባቸው።

1. የአገልግሎት ጽንሰ ሐሳቦች እና አማራጮች ምናሌ ማዘጋጀት።
2. እያንዳንዱ ጽንሰ ሐሳብ የጥናቱን ግቦች እና ኢላማዎች እንዴት እንደሚያሳኩ በዝርዝር ይገልፃል
3. አሁን ያሉትን የ APC ተሳፋሪነት መሰረት በማድረግ አዲስ አገልግሎቶች ላይ የተሳፋሪዎችን ሽግግር መተመንን ጨምሮ፣ አሁን ያሉት ተሳፋሪዎች ላይ ሊያስከትሉት የሚችሉትን ተጽእኖዎች መግለጽ
4. የስርዓቱ አጠቃላይ አፈፃጸም ላይ ሊኖሩ የሚችሉ አፈፃጸሞችን መግለጽ
5. ሊኖር የሚችል ተመራጭ የገበያ ትንተና በመጠቀም፣ በእነዚህ ጽንሰ ሐሳቦች የተነሳ የመጡትን የተሻሻሉ ጉዞዎች (ልክ እንደ የቀነሰ ጊዜ ያሉ) ከፍተኛ መሻሻሎችን መለየት።
6. የገንዘብ ተጽእኖዎችን መግለጽ እና ተጨማሪ የገንዘብ ምንጮች የሚገኙባቸው ዕድሎች ካሉ መወሰን
7. የርእስ 5 አገልግሎት የፍትሃዊነት ትንተና እያንዳንዱ የቀረበውጽንሰ ሐሳብ መሰረት መከናወን አለባቸው።
8. እያንዳንዱ ጽንሰ ሐሳብ ለንጽጽር በሚረዳ መልኩ በማጠቃለያ መቅረብ አለባቸው።
    ሀ. ምርጫ
    ለ. ዝርዝሮች
    ሐ. ውጤት/ወጪ

9. የሚመከረውን ጽንሰ ሐሳብ መጠቆም እና ውስጣዊ እና ውጫዊ ጥንካሬዎች እና ድክመቶችን ጨምሮ ሁሉንም የግምገማ ምክንያቶች መግለጽ እና ማካተት።

## 9. የአገልግሎት እና የትግበራ ዕቅድ

ተመራጩ የአገልግሎት ጽንሰ ሐሳብ የአገልግሎት እና የትግበራ ዕቅድ ላይ በዝርዝር ይቀርባሉ። የአገልግሎት እና የትግበራ ዕቅዱ የተመረጠው የአገልግሎት ጽንሰ ሐሳብ ላይ የታለሙትን የአገልግሎት ደረጃዎች አሁን ባሉት ግብዓቶች እንዴት በተሳካ ሁኔታ እንደሚያሳኩ፣ እና ተጨማሪ መዋዕለ ንዋዮች ሲደረጉ ምን ዓይነት ማሻሻያዎች ሊደረጉ እንደሚችሉ ግምገማ ያደርጋሉ። የአገልግሎት እና የትግበራ ዕቅድ በአገልግሎት ተዋረድ ውስጥ የትኛዎቹ አገልግሎቶች ለስምሪቶቹ ሃላፊነት ያለባቸውን ኤጀንሲዎች ይለያል። በተጨማሪም የሚከተሉትን ያካትታል፦

ሀ. የአገልግሎት ዕቅዱን እያንዳንዱ ምዕራፍ ለማሳካት የሚያስፈልጉ የማሻሻያ ክፍሎችን ይለያል።

ለ. ለሕዝብ ፎረም ተሳትፎ መጣጥፎችን ማዘጋጀት።

ሐ. የትግበራ የጊዜ ሰሌዳ።

መ. አዲስ የአገልግሎት ዕቅድ ለማውጣት የገበያ ዕቅድ ማውጣት።

የአገልግሎት ዕቅዱ የመጀመሪያ ዕቅዱ ላይ ምን ሊስተናገድ እንደሚችል እና ተጨማሪ መዋዕለ ንዋይ የሚጠባበቁ ተከታይ ምዕራፍች ላይ መተግበር የሚገባቸውን የመሰረተ ልማት እና የቴክኖሎጂ አቅሞች ላይ ግምገማ ያከናውናል። ዕቅዱ የትግበራ የጊዜ ሰሌዳ አካል በመሆን የጊዜ ሰሌዳዎችን (ልክ እንደ የአጭር ጊዜ፣ የረጅም ጊዜ) ያካትታል እና በአጭር ጊዜ ውስጥ በትክክል ሊተገበሩ የሚችሉ ስትራቴጂዎች ላይ ትኩረት ያደርጋል።